# ቅኝተ ከራሞት ዘ መቀሌ

## ክፍል አንድ

*(ከቦሌ እስከ አዲ-ሃቂ መቀሌ)*

በተለያዩ ትውልዶች ዘመን የኢትዮጵያ ህዝቦች ማህበረሰባዊና ሀገራዊ ሕይወት እና መሰረታዊ ተፅዕኖ በማሳረፍ አቅጣጫ የቀረፁ ክንውኖች፣ ድርጊቶችና ሂደቶች በተጨባጭ ፈልቀውባታል፤ እንደ ታሪክም አሻራቸው በመሆን ከትውልድ ትውልድ የሚያስታውሱን ቅርሶች አምባ ናት፡፡ ትግራይ ክልል፡፡ ይህም ሆኖ የትግራይ ህዝብም ሆነ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጥንታዊ፣ የትላንት እና የዛሬ ታሪክ ወንዞች በአንድ ይፈስሱባታል፡፡ የአንድ ወርቃማ ዘመን ፈጠራና ስልጣኔ አመላካች አክሱም፣ ነጃሻና ደብረዳሞ፤ አቅምና ኃይልን የተመካ እብሪታዊ የውጭ ወረራን በፅናት ያመከነ ተጋድሎና ጀግንነት አድዋ፣ ተምቤን፣ ሽሬ፣ ዳእሮተኽሊ ወ.ዘ.ተ...፤ ስርዓታዊ ተገላይነትና በደል ከጦረኝነትና ከተፈጥሮ ጋር አብሮ ያስከተለው እልቂትና ውድመትን በመወከልም የ1966ና 1977 ረሃብ፣ የ1935 የአፄው መንግስት የመቀሌ ድብደባ፣ የደርግ የሐውዜን ጭፍጨፋ እና ከተሸከሙት የልጅነት ንፅህናና ይዘውት ከነበረው እርሳስ ውጭ ምንም የሌላቸው ህፃናትን የቀጠፈው የሻእቢያ የአይደር ድብደባ ይህን የቅርብና የሩቅ ታሪክ ሂደት የሚወክሉ ጅረቶች ናቸው፡፡

ከገበሬዋ የእምነት ጓዳ ጠንካራ መንፈስን፣ ከማጀቱ ብርታት የቻረ ጉርስን፤ በጋራና ሽንተረሮቿ ለልጆቹ ያደላ ጋሻና ከለላነትን በመስጠት፣ ፍሬዋን መስዋእት ለሚያደርግ ተጋዳይነት መርቃ በምትልክ እናት አጅበው ትግራይ እና ትግራውያን የትላንቶቹንም ሆነ የቅርቦቹን የነፃነትና የመብት ተጋዳይ የኢትዮጵያ ልጆች ሰማእትነት ምጥ አምጠው ተጋርተዋል፡፡ ባላመነታ ፅናትም ከመሰል የኢትዮጵያ ወንድሞችና እህቶቻቸው ጋር ሆነው ድልን አዋልደዋል፡፡ የአፄ ዮሐንስና የምኒልክ ሰራዊት የትላንት ድል፣ በሽንተረሮቿና ዋሻዎቿ በበቀለው ቀዳማይ ወያነ፣ ዳግማይ ወያኔ ብሎም ኢህአዴግ ግንባር ቀደምትነት ፋሽስታዊውን ደርግ አንኮታኩቶ የዘመነ አድልኦና አፈናን ፋይል ከኢትዮጵያችን ፊት ዘወር ያደረገው የግንቦት 20 ድል፣ ከየማዕዘኑ በተመሙ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ልጆች ደም የተዋለደው የባድመ፣ ዛላአምበሳ፣ አይጋና አሊቴና ተራሮች የሚመሰክሩለት የቅርቡ ፀረ ሻእቢያ ድል የዚህ እውነት ሐውልቶች ናቸው፡፡

በኢኮኖሚው ልማት የተገኘውን እመርታ ለመቀጠልና ለማዝለቅ እንዲሁም አስተዳደራዊ በሆኑ የአፈፃፀም እና ወይም የግንዛቤ/አመለካከት ችግር የተነሳ ህገ መንግስታዊ ዋስትና ያለው የኢትዮጵያ ህዝቦች ስርዓታዊ ባለቤትነትና ተያያዥ መብት ሳይሸራረፍ እንዲከበር «እመርታ በመልካም አስተዳደር» በሚል መሪ ቃል ስር የተካሄደው 6ኛ ጉባዔ ዋነኛ አስተናጋጅ የሆነችው መቀሌ ከፍ ሲል የጠቀስነው የኢትዮጵያ የትላንትና የዛሬ ታሪክ ተቋዳሽና ህያው ዋቢ ናት፡፡ አለፍ ሲልም የነገዋ

ኢትዮጵያ ህልምና ጉዞን ገላጭ የሆኑ ተጨባጭ እውነታዎች ያሉባት ከተማ ነች። የአንድ መቶ ሰላሳ አምስት ዓመታት እድሜ፣ የሩብ ሚሊዮን ነዋሪዎች ባለፀጋ የሆነችው መቀሌ የከበቧት ተራሮች፣ ግንባታዎች፣ ከትላንት ተላልፈው ለዛሬ የበቁ ውርሶቿ እና በውስጧ ያቀፈቻቸው ሰፈሮችና ዋና ዋና ተቋማት ያላቸው ስያሜ ካለተንታኝ ይህን የትላንት፣ የዛሬና የነገ ኢትዮጵያችን እውነታ ይገልፃሉ።

ከአምባላጌ በሽንፈት ለማፈግፈግ የተገደደው ጣሊያን የመጨረሻውን የሞት ሽረት ውጊያ ያደረገበት እንዳየሱስ ተራራ መቀሌን በኩራት ደረቱን ገልብጦ ይመለከታል። ይህ ኩራት ግን ከትላንት ታሪክ ብቻ የመነጨና በዚህ ብቻ የደመቀ አይደለም። እንዳየሱስ ተራራ ዛሬ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች የመጡ ወጣቶች ዘመናዊ እውቀት አብረው እየተቋደሱ የጠነከረ አንድነት መሰረት የሆነውን ተጨባጭ ትውውቅ፣ መግባባትና ውህደትን ማጎልበት ያስቻላቸው የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አምባ ነው። እናም እንዳየሱስ ዛሬ ህያው በሆኑ የሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ልጆች ውበት የሞቀ፣ በነገዋ ኢትዮጵያ ተስፋ የደመቀ የትላንቷ፣ የዛሬዋና የነገዋ ኢትዮጵያ በአንድ ተዋህደው በቀረቡበት መድረክነት የሚመሰል ቦታ ነው።

በ1935 የአዬውን መንግስት፣ በ1990 ደግሞ የሻእቢያን ቦምብ ያስተናገደችው እንዲሁም ከ1970ዎቹ ጀምሮ እስከ 1980 በዘለቀው የደርግ አፈናና ጦረኝነት የእነ ለገሰ አስፋው ካምፕ በመሆን ያገለገለችው የመቀሌ ከተማ መሀልም ዛሬ በከተማዋ ንግድ ምክር ቤት በመገንባት ላይ የሚገኘው ዘመናዊ የገበያ ማዕከል እና ወደ ኮሌጅ ደረጃ ሊያድግ የበቃ አይደር ት/ቤትን የያዘች ሆናለች። በድንጋይ ካብ በተሰሩ የጥበቃ ማማዎችና በእሾሃማ ሽቦ ላይ ተለጥፈው በሚንቀጫቀጩ ቆርኪዎችና ጣሳዎች ተከብበው የእነ ለገሰ አስፋው የግርፊያ እና የጦር ማዕከል መገልገያ በነበሩ የመቀሌ ቦታዎች ላይ ከሰላሳ በላይ የግል ኮሌጆች፣ የኮምፒውተር ስልጠና ት/ቤቶች፣ ጉባዔተኛ ውን ያስተናገዱ ዘመናዊ ሆቴሎች ወ.ዘ.ተ... ተገንብተው ቆመዋል። የዛሬዋ መቀሌ የጦረኝነት ሳይሆን የልማትና የተስፋ አምባ መሆኗን በመመስከር አይነት።

የሰማእታቱን ተጋድሎ ግዙፍነት ባይተካም በዝክሩ ውስጥ ሊካተት የሚገባው ምስላዊ ክብርና ግርማሞገስ በቆመው ሐውልትና ተያያዥ ሆነው በተሰሩት የጉባዔ አዳራሾች፣ መፅሐፍት ቤት፣ ሙዚየም እና የካፍቴሪያ ህንፃዎች ውስጥ ይንፀባረቃል። ይህ ከየትኛውም የመቀሌ ክፍል ሆነው ማየት የሚችሉት የትግራይ ሰማእታት መታሰቢያ ማዕከል የኢትዮጵያ ሕዝቦች በጋራ፣ ትግራውያንም በተናጠል ከየት ተጉዘው የት እንደደረሱ እና ወዴትም እንደሚሄዱ የሚጠቁም ህያው ታሪክ በአንድ ማዕድ የቀረበበት ገበታ ተደርጎ ሊታይ ይችላል።

ይህን ጨምሮ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ህግ ፋኩልቲ ካምፓሶች እንዲሁም በቅርቡ ተገንብተው የተጠናቀቁና በስፋትም በመገንባት ላይ የሚገኙ ውብ የግል መኖሪያ

ህንፃዎችን በመቀሌ እቅፍ ውስጥ ሆኖ የያዘው ሰፈር በርዕሳችን የጠቀስነው አዲ ሃቂ የተባለ ቦታ ነው። አዲ ሃቂ ማለት የሃቅ ወይም የእውነት መንደር፣ ሰፈር ወይም እንደመጠኑ ሀገር ማለት ነው። የዛሬዋን ኢትዮጵያ እውን የማድረግን ትግል ለመቀጠል ከዛሬ 18 ዓመት በፊት ተምቤን በሚገኝ አንድ ዋሻ ውስጥ የተሰባሰቡ የኢህዴን (ዛሬ ብአዴን) እና የሕወሓት አባላት ከተገናኙበት መስራች ጉባዔ ወዲህ የኢህአዴግ ጉባዔ በትግራይ ምድር የተካሄደው ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነበር። የአዲሃቂና የጉባዔው ቁርኝት በህይወት ቆይተው ይህን በእርካታ እንዲሁም በተለዩዋቸው ጓዶች ትውስታ ለሚመለከቱም ሆነ ለእኛ መሰል ታዛቢ እንግዶች ተምሳሌያዊነቱና ገላጭነቱ የከበደ መልእክትም አለው። ከጉባዔው ዓላማ፣ ከነበረው መንፈስና ብሩሐማነት ጋር እንዲጣጣም የታቀደ በሚመስል መልኩ ይኸው ለኢህአዴግ 6ኛ፣ የነፃነትና የእኩልነት ምድር በሆነች ፌዴራላዊት ኢትዮጵያ ስር ለምትገኘዋ አዲሲቷ ትግራይ የመጀመሪያ የሆነው የኢህአዴግ ጉባዔም የተካሄደበት የሰማእታት ማዕከል እንደጠቀስነው የሚገኘው በዚሁ የሃቅ/የእውነት ሰፈር ውስጥ መሆኑ ነው።

አፍጥጦ የሚታየውን የዛሬ ህያው የለውጥና የልማት እውነት፣ እዚህ ለመድረስ የተከፈለውን መስዋእትነት መጠን የሚያስታውሱ የታሪክ እውነቶች እና ህያው ምስክሮችን መካድም ሆነ ያልሆነውን ፈብርኮ መዋሸትም ይተናነቃል። በደርግ አጠራር «ቀበሌ 14» በተለምዶ ደግሞ «እንዳ አቦይ ፈቃዱ» በመሳሰሉ የመቀሌ ሰፈሮች ውስጥ ነዋሪ ከሆኑና በትግሉ ልጆቻቸው፣ ወንድሞቻቸው/እህቶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው የተሰዉባቸውን ሕያው ዜጎች አይተው፣ ተገናኝተውና እጦቱ ባልቀነሰው ፍቅራቸው ተስተናግደው ባለበት ሁኔታ ደግሞ ጭርሱኑ አይሞከርም።

ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይ ሲበሩ በአመዛኙ ባዶ ሆነውና አግጥጠው የሚታዩት የሰሜን ሸንተሮችና ሜዳዎች ዘንድሮም አረንጓዴ ለብሰውና ትኩስ ታርሰው ይታያሉ። ከሰባት ዓመታት በፊት በዚሁ ወርሃ መስከረም ተመሳሳይ በረራ አድርጌ ካየሁት ጋር ፍፁም አይመሳሰልም። በእርግጥም ተፈጥሮ ለተያዘው የልማት፣ የተሻለ ህይወትና የበለፀገ ሀገር የመፍጠር ጥረትና ህልም ወግናለች ያሰኛል። አስራ አንድ ሰዓት ከአስራ አምስት መቀሌ ለማረፍ በተቃረብንበትና አውሮፕላኑ ወደ መሬት ባዘቀዘቀበት ወቅት በመስኮት በኩል የቃኘሁት የመቀሌ ዙሪያ አካባቢም ቡቃያ፣ ዛፍ፣ ሳር ወ.ዘ.ተ... በፈጠረው አረንጓዴማነት ተሸፍኗል። በ1992ዓ.ም በቆርቆሮ በተሰራ ጊዜያዊ ማስተናገጃ የተቀበለኝና በወቅቱ በግንባታ ላይ የነበረው የአሉላ አባ ነጋ አውሮፕላን ማረፊያ ተጠናቅቆ ለዓለም አቀፍ በረራ በሚመጥን ደረጃ የተዋበና የተደራጀ ሆኗል።

የመቀሌና ዙሪያዋ ነዋሪዎች በተመሳሳይ ወቅት በነጠላና ጋቢያቸው ሳይቀር ድንጋይ እያመላለሱ ሲደለድሉ፣ ሲቆፍሩና ሲመነጥሩት የነበረው ከአውሮፕላን ማረፊያው ወደ መቀሌ እምብርት የሚያመራው የአስፋልት መንገድ ግንባታም ተጠናቅቆ

ምቹቱን ተጉገዩ አጣጣምኩት:: በግራ፣ በቀኝና በመሀል በመስመር ሆነው በሚታዩ ተክሎች ይበልጥ ድምቀትንም ተጎናፅፎ ከመቀሌ የአመሻሽ ነፋሻማነት ጋር ውብ ውህደት ፈጥሯል:: ከሰማይ ቃኝቼው የማረከኝን ቡቃያና ልምላሜ መሬት ረግጬ በቅርበት ሆኜ እውን መሆኑን አረጋገጥኩ:: የጠቀስኩትን የተፈጥሮ ደግነት ተጠቅሞ የእጥረት ወቅትን ሊገራ በቻለ ተጨባጭ የልማት ስራ እውን ሊሆን እንደቻለም በመቀሌ አቅራቢያ የሚገኙትን የአብርሃ አፅብሃ እና ራያ ገበሬዎች ሰፈር በማየት ተገነዘብኩ::

በችግርና በረሃብ ሲያዝ መሸጥ ወይም አርዶ መብላት አምሮት ያሉትን የተወሰኑ ከብቶች አጣለሁ በሚል ፍርሃት ከንብረትነት ይልቅ ልጅነታቸው እንዲያመዝንበት «ኩሁሎ» ወ.ዘ.ተ... እያለ በሬውን ሲጠራ የኖረ ገበሬ ዛሬ ቁጥራቸው በዝቶለት የሀብትና የገንዘብ ምንጭ አድርጎ መመልከት እንደጀመረም ተረዳሁ:: የቆፈራቸውን የጉድጓድ ውሃ ማጠራቀሚያዎችና ማቆሪያዎች ተጠቅሞ በዓመት አራት ጊዜ ማምረት ወደ መቻል ተሻግሮ ጥሪት የቋጠረ ገበሬ ሆኗል:: ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ብድር መጠየቅ፣ ባንክ ብር ማስቀመጥ፣ የውሃ ሞተርና የድሪፕ ቴክኖሎጂ መጠቀም፣ ጀነሬተር ገዝቶ የኤሌክትሪክ ብርሃን ተገልጋይ መሆን እና መኝታውና ማብሰያው የተለየ የሆነ ክፍሎች ያሉት መኖሪያ ባለቤትም ሆኗል:: የመቀሌ አካባቢ ገበሬ:: መንግስትም በየቀበሌዎቹ የስልክ መስመር በመዘርጋቱ ከዘመድ ከመገናኘት አልፎ ወቅታዊ የገበያ መረጃን በማግኘት ላይ የተመሰረተ ሽያጭ ከሚያስገኘው የጨመረ ገቢ ተጠቃሚ ሊሆን በቅቷል:: በአጭሩ የአብርሃ አፅብሃ እና ራያ ቅርብ አካባቢዎች ገበሬ ኮሜርሻል ፋርመር የመሆን ደጃፍ ላይ መቆሙ የማይክዱት፣ አላይም ብለው ቢጨፍኑም የማይፍቁት የገበሬው ህይወት እውነታ ሊሆን ችሏል::

ባለፉት ሶስት ዓመታት በተከታታይ የተመዘገበ የልማት እመርታ ተብሎ በኢህአዴግ የሚጠቀሰው ጉዳይ በእርግጥም በተጨባጭ መሬት ላይ የሚያጋጥም እውነታ ነው:: ይህን በመቀሌ ከተማና በአቅራቢያው በሚገኙ የገበሬ መንደሮች የሚገኝ ህያው እውነት ተመርኩዘው የጉባዔው መሪ ቃል የሆነውን «ልማታዊ እመርታውን በመልካም አስተዳደር እመርታ ደግፎ የማዝለቅና የመቀጠል» ወደ መሬት አውርዶ በተግባር እውን ሲሆን ለማየት ጉጉት ይጨምራል:: ጉጉት ብቻም አይደለም:: በአዎንታዊ ስሜት የተሞላ ተስፋ የታከለበትም ይሆናል::

የአዲሃቂ-መቀሌ 6ኛ ጉባዔ የአዳራሽ ውስጥ ውይይት ሂደት እና በአምስቱ ቀን የታዳሚው አከራረም የተስተዋለው መንፈስስ ምን ይመስል ነበር? በእርግጥ ይህን አዎንታዊነት የታጠቀ ስሜትና መንፈስ ተጋርቶ ያንፀባረቀ ነበርን?

የነዋሪዎቿን ልብ እና ጓዳ ማስመሰልም ሆነ ስስት ባልነካው ቸርነት በመክፈት ላስተናገደችን የአዲሃቂ፣ የአዲፍቅር እና የአዲ አዲስ አንድነት ከተማ ለሆነችው መቀሌና መቀሌያውያን ምስጋናና አክብሮቴን ልግለፅ፡፡ በቀጣዩ የፅሑፋችን ክፍል «እመርታዊ እይታችን» ይቀጥላል፡፡ እናም በቆይታችን ወዳስተዋልነው የኢህአዴግ የእመርታ ጉባዔ ሂደት፣ የኢህአዴጋውያን የዚያ ሰሞን እመርታዊ ውሎና እመርታዊ ምሽት ላይ ትኩረት ያደረገ ዘገባ ይቀርባል፡፡